# ሠ ቅ ዷ ሊ

የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (ዐኅኢአድ) ልሣን

የዐማራ ኅልውና መጠበቅ፣ ለኢትዮጵያ አንድነት መጠበቅ ዋስትና ነው!



ፈለገ አሥራት የትውልዳችን ቃል ኪዳን ነው!

ቅጽ: ፩ ቁጥር: ፱ ቀን: መጋቢት ፮/፲

በየ15ቱ ቀን ዘወትር ኀሙስ የሚወጣ


## *የወያኔ ውድቀት ኢትዮጵያን በመበተን እንዳይጠናቀቅ እንጠንቀቅ!*

አባቶቻችን «የሚያድግ ጥጃ ከገመዱ፣ የሚያጠገብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል» ይላሉ። የትግሬ-ወያኔ የማያድግም የማያጠግብም መሆኑ ከጅምሩ የሚታወቅ ነበር። የዚህ ማሳያዎቹ የኢትዮጵያን ታሪክ በመቶ ዓመት መገደቡ፣ የኢትዮጵያዊነት መነሻ ከሆኑት አንዱ የሆነውን ክፍለሀገር ባሕረነጋሽን (ኤርትራ) በኢትዮጵያ ቅኝ ተገዥነት የተያዘ ነው ብሎ ተዋግቶና በኋላም ፈቅዶ ማስገንጠሉ፣ ኢትዮጵያ አንድ ሀገርና አንድ ኢትዮጵያዊ የዜግነት መገለጫ የላትም በማለት ሕዝቡን በነገድ መከፋፈሉና «ሕዝቦች» እያለ መጥራቱ፣ አገሪቱን ወደብ አልባ ማደረጉ ለአብነት የሚጠቀሱ ናቸው።

ወያኔ ከመነሻው ፀረ-ኢትዮጵያ ከመሆኑም በላይ፣ የአገዛዝ ዕድሜው ማራዘሚያ አድርጎ የተከተለው ስልት፣ ኢትዮጵያን ፣ኢትዮጵያ ያሰኟትን የዐማራና የኦሮሞ ነገዶች ከመከፋፈል አልፎ፣ በጠላትነት ግራና ቀኝ እንዲቆሙ ለማድረግ ብዙ ርዕቀት የተጓዘ የመነጣጠል ሥራ መሥራቱ አንዱና ዋናው የአገዛዙ ዕድሜ ማራዘሚያ እንደሆነ ይታወቃል። በፀረ-ኢትዮጵያ አቋሙም በመግፋት ትውልዱ የአገሪቱን ታሪክ እንዳይማር ማገዱ፣ የአገሪቱ የወል ዕሴቶች የሆኑት፦ ተስፋ፣ ልምላሜና ሀብት፣ሃይማኖት፣ አበባና ፍሬ፣ ፍቅር፣ መስዋዕትነትና ጀግንነት፣ የአረንጓዴ፣ ብጫ እና ቀይ ቀለም ሰንደቅ ዓላማችን ትርጉሙም መሆን ያበሳጫቸው የባንዳዎቹ ልጆች፣«ችግራችን ከቀለሙ ሳይሆን፣ ከቀለሙ ጀርባ ያለው ነው» በማለት ይህን የሚያጠፋ የሰይጣን አምላኪዎች ምልክት የሆነውን የሉሚናቴ ምልክት ወይም ሕዝቡ በተለምዶ «አምባሻ» እያለ የሚጠራው ምልክት ከመሐሉ ላይ ማሳቀመጡ፣ ለኢትዮጵያ አንድነትና አገራዊነት ጠላትነት አቋሙ ግልጽ ማሳያ ነው።

እነዚህን ድርጊቶች በጥሞና ስንመረምር የትግሬ-ወያኔ ጅምር ዘላቂ አለመሆኑ የተከተለው የሕዝብና የመንግሥት አደረጃጀት፣ያቀነቀነው የዘረኝነት ዕዕዮተ-ዓለም፣ይህን ተከትሎም በዐማራው ላይ የፈጸመው የዘር ማጥፋትና የዘር ማጽዳት ወንጀል፣ በአኙዋክ እና በኦሮሞ ነገዶች ላይ የፈጸመው የዘር ጥቃትና ማፈናቀል ከቧት ጤዛነት ያለፈ ዕድሜ እንዲኖረው የሚያስችል እንዳልሆነ ድርጊቱ አመላካች ነበር።

# የወያኔ ውድቀት ኢትዮጵያን በመበተን እንዳይጠናቀቅ እንጠንቀቅ!

«ሥራ ለሠሪው፣ እሾህ ላጣሪው» እንዲሉ፣ ይኸውና የትግሬ-ወያኔ የዘራውን እየሰበሰበ ነው። ኢትዮጵያውያንን በነገድ ለመለያየት ሆን ብሎ ያራገበው እሣት፣ አራጋቢውን ከመለብለብ አልፎ እያቃጠለው ይገኛል። በዘረኝነት ኮትኩቶ ያሳደገው ትውልድ እሳት ለብሶ፣ እሳት ጎርሶ ወያኔን መግቢያ መውጫ እያሳጣው ይገኛል። ይሁን እንጂ፣ ወያኔ ዘረኛና አጥፊ ቡድን መጥፋት ያለበት ስለመሆኑ፣ ዕውነተኛ ኢትዮጵያውያን የሚያስደስታቸውን ያህል፣ የወያኔ ወድቀት የኢትዮጵያን መበታተን እንዳያስከትል የሚሰጉ መኖራቸው ደግሞ ግልጽ ነው። ፤ይህ ሥጋት ከምንም የመጣ አይደለም። የሥጋቱ ምንጭ፣ በ«ቄሮ» ስም የሚጠሩ ስብሰባዎች፣ ሕዝባዊ ተቃውሞዎችና ሰላማዊ ሰልፎች ላይ  የሚታዩት ሰንደቅ ዓላማዎች የኢትዮጵያ ካለመሆናቸውም በላይ፣አቶ ለማ መገርሣ ካስተጋቡት ኢትዮጵያዊነት ስሜት ጋር የሚጋጩ  መሆን ያሳደረው ሥጋት አለ።   ይህ ደግሞ ትክክለኛ ስጋት ነው።

የትግሬ-ወያኔ ከሶማሊያ ነፃ አውጭ ድርጅት ጋር ያደረገው ስምምነት፣ የኦሮሞ ተዋቃውሞ ከዐማራው ጋር መተጋገዝ ካስከተለው የተቃውሞ ተከታታይነት እና በወያኔ አገዛዝ ላይ ካሳደረው ተጽዕኖ አኳያ የሚታይ ነው። ዛሬ በወያኔ መወደቅ ዋዜማ የሚታይ የስልጣን ርክክብ ከዚህ በፊት በሀገራችን ላይ የደረሰውን የክህደት ተግባር ደግመን እንድናይ የሚያደርግ ይመስላል።ዛሬ ያለው የስልጣን የርክክብ ሽርጉድ የጠቅላይ ሚኒስትሩን ቦታና ቁልፍ የሲቪል የሚኒስቴር ቦታዎችን ለኦህዴድ ለመስጠት ያለመ መሆኑ ያደባባይ ሚስጢር ነው። ታዲያ ኢትዮጵያ እንደሀገር እንድትቀጥል ለምንፈልግ ኢትዮጵያውያን ስጋታችን ወያኔ ለኤርትራ መገንጠል ቀድሞ ዕውቅና ከመስጠት ባሻገር ለኤርትራ መገንጠል እና ራሷን የቻለች አገር እንድትሆን ዕውቅና እንድታገኝ ለተባበሩት መንግሥታትና ለአፍሪካ ኅብረት ደብዳቤ እስከመጻፍ የደረሰ መጥፎ ታሪክ የሚረሳ አለመሆኑ ነው።  ዛሬም ከወያኔ ትግሬ የመገንጠል የጧት ህልም አኳያ ኦሕዴድም ተመሳሳይ ሥራ እንዲሠራ የታቀደ ይመስላል። «ጠር ጥር፣ ከገንፎም አይጣፉም ስንጥር» ነውና ወገኖች ድርጊቱንና ሂደቱን በቅርብ በመከታተል ፣የምንመኘው ቀርቶ፣ የፈራነው እንዳይደርስ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅብናል። በወያኔ ውድቀት፣ ኢትዮጵያ እንድትበታተን ልንፈቅድ አይገባም።

ዛሬ በህዝባችን ከዳር እስከ ዳር የተቀጣጠለው እንቅስቃሴ ለመሰረታዊ ለውጥ የሚደረግ እንቅስቃሴ ነው። ይህ  መሰረታዊ ጉዳይ በሁሉም ጠቃዋሚነን በሚሉት ዘንድ አጥብቆ ሊያዝ ይገባል። እዚህ ላይ ብዥታ ካለና አቋርጭ መንገድ በመፈለግ ለስልጣንም ሆነ ለመገንጠል የሚደረግ ሙከራ ሀገሪቲን ወደማይፈለግ የርስ በርስ ጦርነት ውስጥ መክተት ይሆናል። መላምቱን በሁለት አኳያ ማየት ይቻላል። የመጀመሪያው መላ ምት ከኦህዴድ ጠቅላይ ሚኒስቴር ማድረግ የሕዝቡን ተቃውሞ ያስታገሳል ተብሎ ከሆነ፣ የሕዝቡ ጥያቄ መሠረታዊ ለውጥ ነውና ተቃውሞውን ሊያስታግስ ፈጽሞ አይችልም። ከአገሪቱ ችግሮች ግዝፈት አኳያ ኃይለማርያምን በለማ ውይንም በሌላ በመቀየር የሚፈታ አይደለም። ሌላውና የምንፈራው መላ ምት ለወያኔ መገንጠል ህጋዊነትን እንዲሰጥ የኦህዴድን ስልጣን ማደላደል ከሆነ ያም ጎዳና የሚወስደን ወደማይቀረው የርስ በርስ እልቂት ነው። ሁለቱም መንገዶች የጥፋት መንገዶች ናቸው።መፍትሔው ሰከን ብለን ለሁላችንም የምትሆን ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን እውን  ማድረግ አማራጩና ብቸኛው፣ አዋጭና ዘላቂነት ያለው ጎዳና  ነው። ይህ ደግሞ  አገዛዙን ከነፖሊሲዎቹ የመቀየር አስፈላጊነት የሚጠይቅ ነው። ዛሬ በኦህዴድ በኩል የተያዘው መንገድ የጥገና ለውጥ መንገድ ነው። ከሱ አፈጣጠርና ጠባብ ጥቅም አኳያም ከዚህ ውጪም አይጠበቅም።

# የወያኔ ውድቀት ኢትዮጵያን በመበተን እንዳይጠናቀቅ እንጠንቀቅ!

ይሁንና ተቃዋሚ ነኝ ከሚለው ጎራ ለኦህዴድ በመስጠት ላይ ያለው ሁሉን ያላገናዘበ ድጋፍ ግን የኋላ ኋላ በወድ የሚያስከፍለው መሆኑን ሊረዳ ይገባል። ተቃዋሚው ትኩረቱ በወያኔና በኦህዴድ መሀል በመካሄድ ላይ ባለ የስልጣን ርክክብ ላይ መሆኑ ቀርቶ ህዝቡ ለመሰረታዊ ለውጥ በሚያደርገው ትግል ላይ መሆን ይኖርበታል እንላለን። ትግሉ ሳይበርድ መቀጠል ብቻ ነው የዚህ ሴራ ማክሸፊያው የሚለውን ቁልፍ የትግል ስልት ልንስተው አይገባም። ሁለቱም የምሰሩት በጥገናዊ የለውጥ ስልት ይህንን የህዝባዊ የመሰረታዊ ለውጥ ትግልን ማክሸፍ ነው። የሁለቱም የጠባብ የፖለቲካ ትግል ግቡን የሚጨበጠው በመሰረታዊ ለውጥ ትግል መክሸፍ ዘንድ መሆኑ የተረጋገጠ ነው።

የታወጀው ያአስቸኳይ አዋጁ ዋና ዓላማ የስልጣን ርክክቡን ተግባራዊ ለማድረግ፣ የህዝቡን የመሰረታዊ ለውጥ ትግልን ለመስበርና ወያኔ የዘረፋቸውን ንብረቶች ወደ ትግራይ የመጓጓዣ ጊዚንና ሽፋን ለማግኘትና የትግራይን ረፐብሊክ የሚለውን ቅዠቱን ዕውን አደርጋለሁ ብሎ የሚያደርገው የጠደፋ ስራ ነው።

እነዚህን ሁኔታዎች አጣምረን ስናይ፣ በተቃዋሚው ጎራ የተሰባሰበ ወገን ነገሮችን በተሳከሮ ሳይሆን በጥሞናና በዋዛ ሊመለከታቸው ይገባል እንላለን። የትግሬ ወገናችንም መሰረታዊ ፍላጎቱ እውን የሚሆነው በመገንጠል ሳይሆን በመሰረታዊ ለውጥ መሰረት ላይ ከምትታነጽ ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ነው የሚል የጸና እምነት አለን። የኦሮሞ ማህበረሰብም እንዲሁ መሰረታዊ ሁለገብ ፍላጎቱ እርካታን የሚያገኘው የጀመረውን የመሰረታዊ የለውጥ ትግሉን ከሌሎች ወገኖቹ ጋር በማቀናጀት ገፍቶ ከዳር ሲያደርሰው ብቻ ነው ።ከዚያ ርቀት በመለስ የሚደረግ ትግል በሱ መሰረታዊ ጥቅሙ ላይ ያነጣጠረ ሴራ መሆኑን እንዲያውቀው እንወዳለን። የወያኔ ውድቅት እውን እንዲሆን እንስራለን። ይሁንና ይህ የወያኔ ውድቀት የምንመኛትን ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን እውን ሳያደርግ በተቃራኒው ወያኔ የታገለለት ኢትዮጵያን የመበታተን ዓላማ ማስፈጸሚያ እንዳይሆን ኢትዮጵያውያን አጥብቀው ሊያስቡበት ይገባል። ስሕተት በስሕተት አይታረምምና ከስሕተት የምንወጣበትን መንገድw መሻት ጊዜ የሚሰጠው ጉዳይ መሆን የለበትም።

የዐማራ ኅልውና መጠበቅ፣ ለኢትዮጵያ አንድነት መጠበቅ ዋስትና ነው!

ኢትዮጵያ በጀግኖች ልጆቿ አንድነቷ ይጠበቃል!